በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.181649

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ደጋረጋ ሙሉ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዉብናት ላቀ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተጠሪ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር አመልካች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የአሁን ተጠሪ በሥር በወረዳዉ ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከአሁን አመልካች ጋር ያለን ጋብቻ እንዲፈርስ፣ በጋራ የፈረናቸዉ ንብረቶች እንዲንካፈል በማለት ዘርዝራ በማቅረብ እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ባቀረቡት መልስ ተጠሪዋ ባቀረበችዉ የንብረት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ክርክር ያቀረበ ሲሆን፤ በራሱ በኩል ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከተጠሪ ጋር ሊንካፈል ይገባል የሚላቸዉን ንብረቶች በመዘርዘር በመጠየቅ፤ የሰራተኛ እዳ አራት ኩንታል በቆሎ አንድ ኩንታል ዳጉሳ፣ አንድ ኩንታል ጓያ አለብን ልንከፍል ይገባል በማለት ጠይቋል። የአሁን ተጠሪ በዚህ በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ መልስ ያቀረበች ሲሆን፣ የሰራተኛ የጋራ እዳ አለብን በማለት የቀረበዉም ሐሰት ነዉ፣ ይህ ተቀጠረ የተባለዉ ልጅ የአሁን አመልካች የግል ልጅ ነዉ የእኔም ሶስት ልጆች የግል ነበረኝ የግል ከብቶች ነበራቸዉ እነዚህ ልጆች አብራዉ ከእኛ ጋር ያደጉ ሲሆን ለሰሩበት ልንከፍላቸዉ አልተስማማንም አልቀጠርናቸዉም፣ የአሁን አመልካች ልጅ እንደልጅ ከቤት ነበረ እንጂ የተቀጠረ አይደለም።

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት የጋራ ዕዳ በማለት ያቀረበዉ የሰራተኛ እዳ 6 [ስድስት] ማዳበሪያ እህል በጋራ ሊከፍሉ ይገባል፤ የባልና ሚስት ንብረቶች ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል። የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበችዉ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የባልና ሚሰት ንብረት በተመለከተ በተወሰኑ ንብረቶች ላይ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ አጣርቶ እንዲወስን የመለሰ ሲሆን፣ የሰራተኛ ዕዳ የተባለዉን የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተ የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ለአራሽ ሠራተኛ አበል የተባለዉን 6 [ስድስት] ማዳበሪያ እህልን በተመለከተ የእርሻ ሥራ ሰራሁ የሚለዉ ግርመዉ ደጋረገ የተባለዉ ሰዉ ቀርቦ ሳይጠየቅ የአሁን አመልካች መብት የለዉም እና ስለ ግርመዉ ደጋረጋ ዉክልና ባልያዘበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ ለአራሽ አበል ከሆነዉ 6 [ስድስት] ማደበሪያ እህል ዉስጥ እዳ በመሆን ድርሻዋን ትክፈል በማለት በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የአሁን ተጠሪ ይህን ዕዳ ልትከፍል አይገባም፣ የጋራ ንብረቶችን በተመለከተ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ በመስጠት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻሻል ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ06/10/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የሥር ፍ/ቤት የሰራተኛ ደመወዝ 6 ማዳባሪያ ሰብል እዳ የአለብን ስለመሆኑ በግራ ቀኝ ምስክሮቻችን ተጣርቶና ተረጋገጦ እያለ ተጠሪም ይህን አምናበት የሰራተኛ ደመወዝ ሰብሉን የከፈለች ሆኖ እያለ

የሥር ፍ/ቤቱ ግን የሰራተኛ ደመወዝን እዳ ያለብንን ባለገንዘቡ ከሶ ይጠየቅ በማለት ለሌላ ወጭ በሚደረግ መልኩ በምስክሮቻችን የተረጋገጠዉን እዳ ዉድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻልኝ በማለት በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ቅሬታዉን አቅርበዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለእርሻ ሰራተኛ የተከፈለ እዳን በድርሻዋ ለአመልካች ልከፍላት አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ6/2/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሰራተኛ ደመወዝ የተባለዉን በድርሻዋ ለአሁን አመልካች መክፈል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢና ሕጋዊ ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ክርክሯን አቅርባለች። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልሰ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የእርሻ ሥራን ለሰራልን ለአቶ ግርማዉ ደጋረጋ ሊከፈል የሚገባዉን ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ሊትከፍል ይገባል በማለት ዳኝነት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ መታያት የለበት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል። እንግዲህ አቶ ግርማዉ ደጋረጋ የአሁን አመልካች ልጅ መሆኑን ከግራ ቀኙ እና ከሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል። አቶ ግርማዉ ደጋረጋ በግራ ቀኙ ተቀጥረዉ የእርሻ ሥራ የሰራላቸዉ ከሆነ እና ሊከፍሉት የሚገባዉ የሥራ ዋጋ ወይም ደመወዝ ካለና መብት አለኝ የሚል ከሆነ አግባብነት ባለዉ የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፣በሕግ አግባብ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚከለክላቸዉ ነገር አልነበረም። የአሁን አመልካች ግን ይህን ግለሰብ ወክለዉ በዚህ ጉዳይ ዳኝነት የመጠየቅና እንዲወሰንልኝ ብሎ ለመጠየቅ በሕግ አግባብ የዉክልና ስልጣን የተሰጣቸዉ ወይም ከሕግ የመነጫ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ከሳሽ ለክስ ምክንያት በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ነገር ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለዉ መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ለመጠየቅ እንደማይፈቀድለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 [2] ሥር ተመለክቷል። በዚህ አግባብ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአሁን አመልካች አቶ ግርማዉ ደጋረጋ የእርሻ ሥራ ስለሰራልን በዚህ ምክንያት ሊንከፍለዉ የሚገባዉን ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን እንዲትከፍል በማለት ስለ

ግርማዉ ደጋረጋ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ጠይቆ እንዲወሰንለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የለም። ስለሆነም የአሁን አመልካች ለሰራተኛ የሚከፍል እዳ ቢኖር እንኳን የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ለገንዘብ ጠያቀዉ እንጂ ለአመልካች የሚትከፍልበት አግባብ የለም፣ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት እና የሥር የከፍተኛዉ ፍ/ቤት አመልካች በዚህ ጉዳይ መብትና ጥቅም የለዉም ብሎ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረግ ሲገባቸዉ የሰጡት ዉሳኔ፣ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር የአሁን አመልካች ስለ ግርማዉ ደጋረጋ ዳኝነት እንዲወሰንለት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም የለዉም በማለት በመረም የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በእርሻ ሥራ ተቀጥሮ አገልግሏል በማለት የጠቀሰዉን አቶ ግርማዉ ደጋረጋ መብት በተመለከተ ይህ ግለሰብ ራሱ ሳይጠይቅ ስድስት ማዳበሪያ እህል እዳ አለብን ከዚህ ዉስጥ ተጠሪ ድርሻዋን ለአመልካች ልትከፍል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።
4. ይህ ችሎት በ27/12/2011 ዓ.ም የሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል። ይጻፍ።

**መዝገቡ ተዘግቷል።**

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ**

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በተመለከተ የአሁን አመልካች የጋብቻ ፍቺ ተከትሎ በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የጋራ የባልና ሚስት ለሰራተኛ የሚከፈል እዳ ያለ በመሆኑ የጋራ እዳ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ የአሁን ተጠሪም አመልካች ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ሲል ያቀረበው እዳ የቀጠርነው ሰራተኛ የለም በሀሰት የቀረበ ነው፣ የባልና ሚስት የጋራ እዳ አይደለም ስትል ተከራክራለች፡፡ የስር የወረዳ ፍ/ቤትም የባልና ሚስት የጋራ እዳ በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ መኖሩን በራሱ በማስረጃ አጣርቶ የጋራ እዳ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም አጽንቶታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባ የአሁን አመልካች ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆን አለበት ሲል ያቀረበው ክርክር ተከፋዩ (ገንዘብ ጠያቂው) ወይም ባለመብት የተባለው ሰው ከባልና ሚስት ገንዘብ አለኝ ብሎ ሳይጠይቅ (ክስ ሳያቀርብ ወይም ጣልቃ ገብቶ ሳይከራከር) የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

የባልና ሚስት የንብረት ክርክር በተመለከተ የክርክር ሂደቱ የቤተሰብ ህጉ በሚደነግገው መሰረት ግራ ቀኙ በዝርዝር በሚያቀርቡት የግል፣ የጋራ ንብረት እና የባልና ሚስት የጋራ እዳ የሆነውን ለይተው ስያመለክቱ ፍ/ቤቱ የህግ ግምት እንዳለ ሆኖ፣ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነው፣ የየግል ንብረታቸውን የሆነውንና የጋራ የባልና ሚስት እዳ የሆነውን በባለሙያ፣ በሽማግሌዎች ወይም በራሱ አጣርቶ የሚወስን ሲሆን፣ የባልና የሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ የተወሰኑ የጋራ እዳዎችም ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ለባለመብቱ የሚከፈል ይሆናል፡፡ ባልና ሚስት በንብረት ላይ ክርክር በሚያደረጉበት ጊዜ ከባልና ሚስቱ ገንዘብ አለኝ የሚል ሰው አንዳንዴ በክርክር ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ከባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸው ገንዘብ እንዳለው ገልጾ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ እንዲወሰንልት የሚጠይቅበት ጊዜ ያለ ሲሆን፣ ባልና ሚስት በንብረት ላይ ክርክር በሚያደረጉበት ጊዜ ከሁለቱ አንዳቸው የባልና ሚስት የጋራ እዳ እንዳለ ከማስረጃ ጋር አስደግፈው ስያመለክቱ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ስታመን በእምነታቸው መሰረት የባልና የሚስት የጋራ እዳ መሆኑን የሚወስን ሲሆን በተካደ ጊዜ በማስረጃ አጣርቶ የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆኑ ከተረጋገጠ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ሲል ይወስናል፡፡ በዚሁ ሁኔታ ሲሰራበትም ቆይቷል፡፡ ይሁንና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የባልና ሚስት ንብረት ተጣቶ የጋራ የባልና ሚስት እዳ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚሁ መሰረት መወሰን ሲቻል ባለመብቱ በክሱ ውስጥ ገብቶ ባለመጠየቁ ጠያቂ የለም በሚል የባልና ሚስት የጋራ እዳ የለም ሲል ውሳኔ መስጠቱ የጋብቻ ፍቺ ውጤት የባልና

ምስት የንብረት ክርክር የንብረት ማጣራት ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በክልሎችም ይሁን በፌደራል የቤተሰብ ህግ የባልና ሚስት የፍቺ ውጤት የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የአማራ ብ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 100 እና የተሻሻለው የፌ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት እዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው እዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሄውም አሰራሩ የተሻሻለው ፌ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83፣ 85 እና ተከታዮቹ በተደነገገው መሰረት የባልና ሚስት ንብረት በባለሙያ፣ በሽማግሌዎች፣ በፍ/ቤት በራሱ ወይም በባልና ሚስት ስምምነት በማጣራት ሲሆን ተጣርቶ በተረጋገጠው መሰረት እዳው የሚወሰን እንጂ ባለመብቱ ጣልቃ ገብቶ ካልተከራከረ በቀር እዳ የለም ተብሎ መወሰኑ የክርክር አመራር ስርዓት ጉድለት ያለበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል እላለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ